# ማተብ እና ስወልቃለን? ሴኩላሪዝምስ ምንድን ነው?

goolgule.com/mateb-and-what-is-secularism/

Editor



**ከአዘጋጆቹ ማሳሰቢያ፤** በዚህ ጽሁፍ ላይ የሰፈረው ሃሳብ በከፊል ወይም በሙሉ የጎልጉል፡የድረገጽ ጋዜጣን አቋም የሚገልጽ አይደለም፡፡ እንደሚዲያ የማንንም ሃይማኖት በመንቀፍም ሆነ በመደገፍ አቋም አንይዝም፡፡ በዚህ ጽሁፍ ላይ የሰፈረው ሃሳብ በሙሉ የጸሃፊው ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው ነው፡፡ ጽሁፉን አስመልክቶ በጨዋነት ማስረጃዎችን በመጥቀስ ለመመለስ ለሚፈልጉ ሁሉ ጎልጉል፡የድረገጽ ጋዜጣ ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኑን ይገልጻል፡፡

---

አሁን በሥልጣን ላይ የሚገኘው አገዛዝ በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ከነሐሴ 18 እስከ መስከረም 16 ድረስ 800 ለሚሆኑ የመካከለኛ አመራሮቹ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሥልጠና በሚሰጥበት ወቅት የእስላም ሴቶች በትምህርት ተቋማትና መንግሥታዊ በሥራ ቤቶች ሂጃብና ኒቃባቸውን እንዲያወልቁ ሲጠየቁ “እኛ እንድናወልቅ የምንገደድ ከሆነ ክርስቲያኑም ማተቡን ይበጥስ” ማለታቸው በተነሣ ጊዜ አቶ ሽፈራው “ማተቡም ቢሆን የጊዜ ጉዳይ ነው እንደ የሃይማኖት መለያ እስካገለገለ ድረስ አደረጃጀታችንን ስንጨርስ ማተብም ቢሆን መውለቁ አይቀርም” በማለት የአገዛዝ ቡድኑ ከክርስቲያኖች አንገት ላይ ማተብ (ማእተብ) የማስወገድ የማስወለቅ አቅድ እንዳለውና ለዚህም አደረጃጀት እየዘረጋ መሆኑን የአብደቱን የመጨረሻ ድርጊት አስታውቋል፡፡ ጥሩ ነው! በግንባራቸው በአንገታቸው በእጃቸው የመስቀል ንቅሳት ያደረጉ እናቶቻችንንና እኅቶቻችንን ለመስቀላቸው እንዴት ተደርጎ እንዲወገድ ታስቦ ይሆን? ቆዳቸውን በመገፈፍ? እየ ምድረ መናፍቅ ለዚህም ተደርሷላ? ግድ የለም አስቀድሞም ቃሉ “ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉና ብዙ ጊዜ ስለ እነሱ አልኋቹህ አሁንም እንኳ እያለቀስኩ እላለሁ መጨረሻቸው ጥፋት ነው ሆዳቸው

አምላካቸው ነው ክብራቸው በነውራቸው ነው ሐሳባቸው ምድራዊ ነው" ፊል.3፤18-19 ይላልና አውሬው በልጆቹ አድሮ ይሄንን ሲያደርግ እንደሆነ በሰማን ጊዜ አልደነቅንም፡፡

በዚህ አገዛዝ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የመናፍቃን ቁጥር አለ፡፡ አገዛዙ እንደዚህ ዓይነቶችን ድርጊቶች መከወን ሲፈልግ የሚጠቀመው እነሱን ነው፡፡ እዚህ ላይ የሰንደቅ ዓላማን አዋጅ ቤተክርስቲያን አስተምህሮዋ ከሚያዛት በተጻራሪ እንዲፈጽም ማድረጋቸውን ያስታውሷል፡፡ እነዚህ ሰዎች ከመናፍቅነታቸውና መናፍቅነታቸው እንዲያደርጉ ከሚገፋፉቸው ጥፋት የተነሣ እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ ሲፈጽሙ በደስታና በነቃ ትኩረት ነው፡፡ እነኝህ መናፍቃን መናፍቃን ቢሆኑም ማተብ ለእኛ ለክርስቲያኖች ምን ማለት እንደሆነ፣ ምንን እንደሚወክል፣ ምን ትርጉም እንዳለውና የአገልግሎቱን አስገዳጅነት አያውቁም ማለት አይቻልም፡፡ ከዚህ የተነሣ አገዛዙም መናፍቃን የአገዛዙ ባለሥልጣናትም የተናገሩት ቃል ምን ያህል ከባድና ምድር የሚንጥ የመጨረሻ ከባድ ነገር እንደሆነ እያወቁ እየገባቸው ትንሽም እንኳን የንዝረት መጠኑ እንዲሰማቸው አልፈለጉም፡፡ በዚህ በማተብ ጉዳይ ላይ ሕዝበ ክርስቲያኑ ሊከፍል የሚችለውን ዋጋ ምንነት አለቅጥ ንቀውና አቅለው ተመልክተውታል፡፡ ለማንኛውም ለሁሉም ሰው ግልጽ ይሆንለት ዘንድ የማተብንና የሂጃብ ሊቃብን ምንነት ማየት ይኖርብናልና ዐንይ ፦

**ማተብ (ማዕተብ) ፦**

ማተብ (ማዐተብ) ቃሉ ግእዝ ሲሆን ዐተበ ከሚለው ግስ የወጣ ቃል ነው፡፡ ዐተበ ማለት አማተበ ባረከ ማለት ሲሆን ማተብ (ማዐተብ) ደግሞ በጥምቀት መባረክን የእግዚአብሔርን ልጅነት ማግኘትን የሚያመለክት ቋሚ ምልክት ማለት ነው፡፡ ማተብ ለእኛ ለክርስቲያኖች የምርጫ ጉዳይ አይደለም፡፡ ወንድ ልጅ በ40 ቀኑ ሴት ልጅ በ80 ቀኗ ቤተክርስቲያን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቃ የእግዚአብሔርን ልጅነት እንድናገኝ ካደረገችበት ቀን ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞታችን ድረስ የሚደረግ ከሞትንም በኋላ አብሮን የሚቀበር ክርስቲያናዊ ግዴታ ያለበት በአንገት የሚታሰር ክርና መስቀል ነው፡፡ የማተብ መበጠስ ወይም መውለቅ ሃይማኖትን የመካድ ተምሳሌታዊ ትርጉም አለው፡፡ አንድ ክርስቲያን በአንድም በሌላም ምክንያት በአርባና በሰማንያ ቀን የታሰረለትን ማተቡን ያወለቀ የፈታ የተወ እንደሆነ ሃይማኖቱን ባይክድም እንኳን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ጥበቃ እንደተለየው እንደሚርቀው ለተለያዩ ዓይነት አጋንንታዊ ጥቃት (ለጸብአ አጋንንት) እንደተጋለጠና እንደሚጋለጥ እንደሚጠቃም ይታመናል ይታወቃልም፡፡ “ልጄ ሆይ! የአባትህን ትእዛዝ ጠብቅ የእናትህንም ሕግ አትተው ሁልጊዜ በልብህ አኑረው በአንገትህም እሰረው ስትሄድ ይመራሀል፣ ስትተኛ ይጠብቅሀል፣ ስትነሣ ያነጋግርሀል፡፡ ትእዛዝ መብራት ሕግም ብርሃን ነውና” ምሳ.6፤19-23 በነገራችን ላይ ማተብ የምናደርገው እኛ ኢትዮጵያዊያን ብቻ አይደለንም ከእኅት አብያተክርስቲያናት (Oriental Churches) ማለትም ከግብጽ፣ ከሶሪያ፣ ከሕንድ፣ ከአርመን በተጨማሪ ላቲኖችም ማተብ የማድረግ ባሕል አላቸው፡፡

አገዛዙ በዚህ ከገፋበት ክርስቲያን ነን ባዮች አባላቱ አንድ አስታራቂ ሐሳብ የሚሉትን ሊያመጡ እንደሚችሉ ይሰማኛል፡፡“ማተብ የሚታየው አንገት ላይ በአጭሩ ወይም ጠበቅ ተደርጎ ሲታሰር ነውና ሰፊ ወይም የማይታይ ማተብ

ክርስቲያን እስላም፣ ሂንዱ ቡድሂ ሳይሉ በእኩል ደረጃ ማስተናገድና ማገልገል የቻለ መንግሥት ወይም ሀገር በምዕራቡ ዓለም እንኳን የለም፡፡ወደፊትም ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም፡፡በተለይ ለእስልምና ያላቸውን ቀትሊ ነገር ከሚችለው በላይ ነው፡፡እስላም የሆነ ሰው ማለብ የሚችል አይመስላቸውም፡፡እስልምናን እንኳን እኩል አድርገው ሲያዩትና ሲያስተናግዱት ይቅርና በተለያየ መንገድ እምነቱን ከሰብአዊነትና ከሞራል ሕግጋት አንጻር እየተነተኑ ያበሻቅጡታል፡፡እንደነ ሳልማን ሩሽዲ ያሉ ደራስያንንም እየተጠቀሙ የእስልምናል መመሪያ ቁርአንን የመጨረሻ ያራከሳሉ ያዋርዳሉ፡፡

ይህ ደራሲ *The Satanic Verses* በሚለው መጽሐፉ ዝርዝር ውስጥ መግባት አልፈልግም እስልምናን እንዳይሆን አድርጎ አዋርዶታል፡፡ኢራን ሳልማን ሩሽዲን በተገኘበት እንዲገደል ፈርዳበታለች ለገደለውም አምስት ሚሊዩን ዶላር እንደምትሸልም ያስታወቀች ቢሆንም እንግሊዝ ግን በልዩ ኃይል አስጠበቀችው፡፡ ምዕራባዊያን ሳልማን ሩሽዲን ኖቬል ብቻ 11 ጊዜ ሸልመውታል፡፡የሌላ ሽልማቱማ ተቆጥሮ የሚዘለቅ አይደለም፡፡ምእራባዊያኑ እንደሚያወሩት ሳይሆን ሴኩላሪዝም ከሽፎ እንዲህ እየታየ እንዳለው እንዲሆን የተገደዱበት ምክንያት የየሀገራቱ ታሪካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባሕላዊና ፖለቲካዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችና አስተሳሰቦችን በዚህ በሴኩላሪዝም የአሠተዳደር ሠርዓት ጋር ማጣጣምና ማስተካከል እንዳይቻል ስላደረገ ነው፡፡



ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

እንግዲህ ሁለንተናዊ አቅም አላቸው ተብሎ በሚታሰቡት በምዕራቡ ዓለም ሀገራት እንኳን የሰው ሁኔታ እንደዚህ በሆነበት ሁኔታ ወያኔ ማን ሆኖ ነው ሲባል ተሰምቶ ጨርሶ ባልገባው ነገር ላይ የሚቀባዥርብን? የለአቅሟና የለምቹ ነባራዊ ሁኔታ ተወጣጥራ ፈንድታ ለመሞት ካልሆነ በስተቀር፡፡ወይ ደግሞ እርስ በእርሳችን የሚያተራምስ የሚያባላ የከፋት የተንኮል የሸር ጥንስስ መጠንሰሳቸው መቀመራቸው መተብተባቸው ሲሆንም ይችላል፡፡እንጅ ወያኔ አቅሙን አያወቀ እንዲህ ዓይነቱን አብደት ይሞክረዋል ብየ አልገምትም፡፡ እንግዲህ ከገፋበትም እንተያያለን!ወንድ የሆነ መጥቶ እንገቴን ይንካ! የወያኔን ጥቅም ለማስጠበቅ የቤተክርስቲያንን የበላይ አሠተዳደር የተቆጣጠሩት ተባብረዋቸው ማተባቹህን ፍቱ በጥሱ ቢሉም እንኳን እንደሚሉም አልጠራጠርም በዚህ ጉዳይ ላይ ሀገር ሳይተራመስ ነገሩም የወያኔ መጥፊያ ሳይሆን አይቀርም፡፡

ቸሩ አምላክ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ደንቀራ መሰናክሉቻችንን ሁሉ አንሥቶ የዚህችን ሀገርና ሕዝብ ክብር ነጻነት ሉዓላዊነት ኃያልነት ይመልስ ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን!!!

ኢትዮጵያ ከሃይማኖቷና ከእሴቷ ሁሉ ጋር በሉዓላዊ ክብር ለዘለዓለም ትኑር!!! አሜን!!!

(ፎቶ: ባለማተብ የትግራይ ሴት)

amsalugkidan@gmail.com